ሰበር መ/ቁ.14414

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ

ስለ አዋጅ ቁ.42/85 ተፈፃሚነት- የአሰሪና ሰራተኛ ትርጓሜ - የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 2/1/፣ 3/2/ /ሠ/

መ/ሰጭ የአዋጅ ቁ. 42/85ን መሠረት በማድረግ አመልካች ይኸንኑ ሕግ ተላልፎ ከስራዬ ያገደኝ በመሆኑ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት በግምቢ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበችውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሉ መ/ሰጭ ከስራ ከታገደችበት ቀን ጀምሮ ያለው ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 39፣40 እና 43 የተመለከተው ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ፍ/ቤቱ

በመወሰኑና ውሳኔውንም የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ችሎት በማጽናታቸው የቀረበ አቤቱታ።

<u>ውሳኔ</u>

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት፣ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የማምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል።

1. አንድ ክርክር በአዋጅ ቁ. 42/85 አግባብ የሚዳኘው በአዋጁ እንደተሰጠው ትርጓሜ አንድ ወገን ተከራካሪ አሰሪ ሌላው ወገን ተከራካሪ ደግሞ ሰራተኛ የሚባሉ ከሆነ ነው።
2. በአዋጁ "አሰሪ" ተብሎ ለሚጠራ "ድርጅት" የተሰጠው ትርጓሜ የሕዝብ አስተዳደር ስራ የሚያከናውኑ አካላት "ድርጅት" ሊባሉ እንደማይችሉ በግለጽ ያመለክታል።
3. በአዋጁ ትርጓሜ "አሰሪ" ተብሎ የማይጠራ "ድርጅት" ጋር የስራ ውል ያለው ሰራተኛ በአዋጁ ትርጓሜ "ሠራተኛ" ሊባል አይችልም።
4. አንድ በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ በመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር አዋጅ አለመሸፈኑ በራሱ በአዋጅ ቁ. 42/85 የሚሸፈን አያደርገውም።

የሰ/መ/ቁ. 14414

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- የጊ.ም.ቢ. ከተማ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት - አላዛር ኢተፋ

ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ- አልቀረበችም፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የግም.ቢ. ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የአዋጅ ቁ. 42/85ን መሠረት በማድረግ የአሁኑ አመልካች ይኸን ሕግ ተላልፎ ከስራዬ አግዶኛልና ኪሣራዬን ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ ስትል በአቀረበችለት ክስ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሥራ ከታገደችበት እለት ጀምሮ ያለው ደመወዝዋ እንዲከፈላት እና ወደ

ሥራዋ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጁ አንቀጽ 39፣40 እና 43 የተመለከተው ካሳ እንዲሰጣት እና እንድትሰናበት ወስኗል።

የወሊጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ውሣኔ ያፀናው ሲሆን በመቀጠል ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የመጨረሻ ፍርድ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል።

ይህም ችሎት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡለትን ክርክር መርምሯል።

ሊፈታ የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ የተከራካሪዎቹ ግንኙነት በአዋጅ ቁ. 42/85 ይሸፈናል? ወይስ አይሸፈንም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል።

በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2/1/ መሠረት አንድ አካል አሠሪ ለመሰኘት በአዋጁ አግባብ ሰራተኛን ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን ይገባዋል። ድርጅት የሚባለው ደግሞ የንግድ፣

የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን ወይም ሌላ ሕጋዊያን ተግባራትን ለማከናወን የተመሠረተ ተቋም መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2/2/ ላይ ተተርጉሟል፡፡ ይኸ ለጅርጅት የተሰጠው ትርጓሜ የሕዝብ አስተዳደር ሥራ የሚያከናውኑ አካላት ድርጅት ሊባሉ እንደማይችሉ በግልጽ ያመላክታል፡፡ በሌላም በኩል የመንግሥት አስተዳደር ሰራተኞች በልዩ ሕግ ከሚተዳደሩ ሌሎች ሠራተኞች ውስጥ የተመደቡ መሆናቸው እና ከአሰሪያቸው ጋር ላላቸው ግንኙነት የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ እንደማይሆን በአንቀጽ 3/2/ሠ/ ላይ ተጠቅሷል፡፡

አመልካች የሕዝብ አገልግሎት ሥራ የሚያካሂድ የመንግሥት ተቋም መሆኑን ከስያሜው እንኳ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጠሪ የቀረበውም ክርክር አመልካች ድርጅት ነው በሚል እና ይህንንም በማስረዳት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ክርክሩ ተጠሪ በመንግሥት ሠራተኝነት የታቀፈች አይደለችም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስም ሠራተኞቹ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ የታቀፉ አልነበሩም ተጠሪ ክስ ከመሠረተች በኋላ የወጣው የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት

ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ቁ. 61/94ም ወደ ኋላ ሄዶ ስለማይሰራ ግንኙነታችን በአዋጅ ቁ. 42/85 የሚሸፈን ነው የሚል ነው፡፡

በዚህ ችሎት እምነት የአንድ ሙግት ይዘት ከአዋጅ ቁ. 42/85 አግባብ የሚዳኝ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በአዋጁ እንደተሰጠው ትርጓሜ አንድ ወገን ተከራካሪ አሰሪ ሌላው ወገን ተከራካሪ ደግሞ ሰራተኛ ሊሰኙ ይገባል፡፡ ከአዋጁ አግባብ ቀጣሪው አሰሪ ተቀጣሪው ደግሞ ሠራተኛ ሊባሉና ሁለቱም በድንጋጌው የተቀመጠውን የትርጓሜ መስፈርት እንዲያሟሉ ያስፈልጋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አሰሪው አመልካች የሕዝብ አስተዳደር ሥራ የሚያካሂድ የመንግሥት መ/ቤት በመሆኑ ድርጅት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አመልካቹ አሰሪ ድርጅት ባለመሆኑም ተጠሪዋ በአዋጁ አሰሪ ከተባለ አካል ጋር የሥራ ውል ግንኙነት ያላት ሠራተኛ ናት ልትባል የምትችል አይደለችም፡፡ ይህ ደግሞ ሁለቱም በአዋጁ የተቀመጠውን ትርጓሜ አለማሟላታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

በእርግጥ ተጠሪ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ያልታቀፈች ሠራተኛ መሆንዋን በመግለጽ መከራከርዋን ተገንዝበናል፡፡ ይህም አዋጁ ተፈፃሚ የማይሆነው በአዋጁ አንቀጽ 3/2/ሠ/ መሠረት

በልዩ ሕግ ለሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች እንጂ ለእኔ በልዩ አዋጁ ላልታቀፍኩት አይደለም በሚል ዓይነት መሟገቷን ያመላክታል። ይሁን እንጂ ተጠሪ እንደምትከራከረው በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጁ የታቀፈች አይደለችም ሊባል የሚችል አይነት ቢሆን እንኳ አለመታቀፉ ብቻውን እርሷን በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ሠራተኛ አመልካቹን ደግሞ ድርጅት ሊያሰኛቸው የሚችል አይደለምና ግንኙነታቸው በተጠቀሰው አዋጅ የሚሸፈን ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርሰን አይሆንም። አመልካች ድርጅት ተጠሪ ደግሞ የድርጅት ሠራተኛ መሆናቸው በአልተረጋገጠበት ሁኔታ የአዋጅ ቁ. 42/85ን ለክርክራቸው ተገቢነት ሊኖረው የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አይኖርም። እንዲሁም ተጠሪ አለኝ የምትለውን የመብት ጥያቄ ለግንኙነታቸው ተፈፃሚ ሊሆን ከሚገባው ሕግ አኳያ አቃንታ ልታቀርብ ከሚገባት በቀር የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ለመብቷ መጠየቂያ ልታደርግ አትችልም። በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የተቀጠሰውን አዋጅ ተመስርተው የሰጡትን ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ፍርድ ይህ ችሎት አልተቀበለውም።

## ው ሣ ኔ

የግምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና በመ/ቁ. 01235 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ.42/85 መሠረት አይተው የሰጡት ከፍ ሲል የተመለከተው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል።